የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሐምሌ 29 ቀን 2000ዓ.ም.

# ሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተመሰረተበትን ሚያዚያ 1964 ዓ.ም. በየአመቱ በመላው አለም በድምቀትና በከፍተኛ ስሜት የሚያከብረው ሕዝብን በመጋበዝና በወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በመወያየት መሆኑ ይታወቃል። ይህንን የምስረታ በአሉን ሲያከብር ኢሕአፓ በኢትዮጵያ የትግል መድረክ ብቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በትግሉ የተገኙ ድሎችና ሽንፈቶችን በመዘከር ብቻ ሳይሆን በትግል የተሰዉ አባላቱን፤ ደጋፊዎቹን በአጠቃላይ ደግሞ በሕዝባዊ ትግሉ መስዋዕትነትን የከፈሉትን ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ በማስታወስና ለወደፊቱም ሕዝባችን የመጨረሻ ድሉን እስከሚቀዳጅ ድረስ ያልተቆጠበ ጥረት ለማድረግ ቃል ኪዳኑን በማደስ ጭምር ነው። ሰማዕታቱ በሕይወት ዘመናቸው የደከሙበት፤ የታገሉበትና ለሕልፈታቸው ዋነኛ ምክንያት የሆነውን የሕዝባችንን ነጻነት፤ እኩልነትና ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዲሰፍን ነው። ይህ የሰማዕታቱ መንፈስ እኛን ቀሪዎቹን ይህንኑ ያስታውሰናል፤ ያስተምረናል፤ ለትግል ይቀሰቅሰናል የመደራጀት ጥሪ ይደውልልናል፤ በቆራጥነት እንድንታገል የመንፈስ ጽናቱን ያላብሰናል።

በመሆኑም ዘንድሮም የ36ኛውን በዓል ቀን ከበፊቱ ለየት ባለ አኳኋን ከታዳሚዎች ጋር ለማክበር በፍራንክፈርት ከተማ በዝግጅት ላይ ይገኛል። በበአሉ አከባበር ወቅት፤

ሀ. ከድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አካል የሆኑት አቶ ፋሲካ በለጠና አቶ ኢያሱ አለማየሁ፤

ለ. ከአለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ድርጅት አመራር ከሆኑት ወ/ሮ አስቴር ደመቀና፤

ሐ. በኢትዮጵያ የሴቶችም ሆነ በሀገር ወዳድ ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉት ወ/ሮ ገነት ግርማ በእንግድነት ተገኝተው ለሕዝቡ ገለጻ የሚሰጡ ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡ የሚቀርብላቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎች ሁሉ በማስተናገድ ሰፋ ያለ ውይይት ይደረጋል። ከውይይቱ በኋላ በታዋቂው ድምጻዊ ተጫዋች ኤሊያስ ተባበልና በሀገር ባሕል ምግብ የታጀበ የመዝናኛ ምሽት አዘጋጅተናል።

በመሆኑም ዝግጅታችን ሁሉንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ይመለከተዋልና ሕዝባችን አሁን ከሚገኝበት አስቃቂና አሳዛኝ ሁናቴ ሊገላገል የሚችልበትን ሃሳብ በማካፈል ለውይይቱ ፍሬያማነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ስብሰባና የጋራ ምሽት በመገኘት ተሳታፊ ትሆኑ ዘንድ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

| | |
|---|---|
| ቦታው | ፍራንክፈርት ከተማ |
| | DB Gastronomie GmbH |
| | Galluspark 2 |
| | Kleyer Str. 21 |
| | 60326 Frankfurt |
| ቀን: | ኦገስት 30 ቀን 2008 ዓ.ም. |
| ሰአት: | ከ13፡00 በአውሮፓ ሰአት አቆጣጠር ጀምሮ |

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

የአውሮፓ ክፍል (የበአል አዘጋጅ ኮሚቴ)

ለተጨማሪ መረጃ 0049 152 07927718, 00312 61052363, 0049 152 04074821 መደወል ይችላሉ።